ሁሉ በእጁ እንዳለ ቢገምት ለራሱ

ጉልበት የ እግዚአብሔር መሆኑን ከረሱ

አዘኔታ ጠፍቶ በግፍ ከረከሱ

ላደረገው ጥፋት ተከፍሎታል ምሱ

ሙሾ ቢወርድለት ቢታዘን ቢለቀስ

አዲስ ሚመጣ እንጂ የሞተው አይ መለስ።

በረከት ተብሎ መርገም ከታደለ

የ አእምሮን ውጤት የ ብዕርን ስራ ሲገድብ ከዋለ

ፍትህ ዲሞክራሲ ነፃነት የታለ።

በዘመነ አዲሱ በ አሮጌው ከሰራ

ከኋላ ወደ ፊት ከፊት ወደኋላ ያለ ምንም ተራ

ይወጣል ይገባል ሊያበዛ መከራ።

ታምራት ጠብቀን ከሆነብን ቁጣ

አገርን ካጠፉ ቦጥቡጦ እንደ አንበጣ

ቢፅለይ ቢሰግድ ምህረት ከ የት ሊመጣ።

ስዩመ እግዚአብሔር በ አገር ባይሰራ

ላይወጣ ላይርቅ ከ ጥፋቱ ሴራ

ጳዉሎስ ወ ማቴዎስ ሆነው ካንድ ጎራ

በሕዝቡ ትከሻ አበዙ መከራ።

አባይ ነው እያሉ ቀሎ ከተገኘ

ወንድሙ  ሲቸገር እርሱ ከተኛኘ

ከ አንድ ዘር መፈጠር ዋጋም አላስገኘ።

ከ አገር ተሰዶ ወጥቶ የ ተገፋ

ለተሻለ ሠላም እንዲህ የሚለፋ

ይብቃ ይቁም ለሚል ግዞት የከረፋ

ይመለሱ ብሎ ጥሩንባ ከነፋ

በጨለማ ይኑር ብርሀነ ይጥፋ።

እርጅና ሲጫነን እድሜአችን ሲገፋ

አእምሮአችን ደክሞ ማስተዋል ከጠፋ

በትልቅ ትንሹ ሰውን ከሚያስከፋ

የቀረበለትን በልቶ ከሚተፋ

ገበታው ተነስቶ ስብሐት ይለፋ።

ቴዎድሮስ ማርቆስ

ከ ኖርዌይ